# <u>ትድረስ በዚህ ዘመን ላላችሁ ካህናት</u>

## <u>ባህታዊ አምኃ ኢየሱስ የመምህር ገብረ ኢየሱስን ድምጽ አሰሙ</u>

ከቀሲስ አስተርአየ ሐምሌ 30 ቀን 2008

nigatuasteraye@gmail.com

በምድራችን ላይ የሚደረጉት ነገሮች በጊዜ፤ በሚፈጸምባቸውና በሚፈጽሙት ሰዎች ይለያዩ እንጅ፤ ድግግሞሽ ናቸው። ባህታዊ አምኃ ኢየሱስ <u>በወያኔ መንግሥት</u> በተበደለው በጎንደር ህዝብ መካከል ቆመው ያሰሙን ድምጽ፤ <u>በጣሊያን ወረራ</u> ጊዜ እነመምህር ገብረ ኢየሱስ ላሰሙት ድምጽ ድጋሚ ነው። ወያኔ በወገን በአገር ላይ የሚፈጽመውን ግፍና መከራ በዝምታ በማለፍ ላይ ያላችሁ፤ ከህዝብ ጋራ አለመታየትን የመረጣችሁ ካህናት ሰባክያንና ጳጳሳትም፤ በጣሊያን ጊዜ ጣሊያንን ላለመስቀየም ዝም ያሉትንና ከህዝብ መካከል የተደበቁትን የካህናትን ዝምታ ደገማችሁ። የተደገመ ነው ብልም፤ ወያኔዎች በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚፈጽሙት መከራና ግፍ፤ ጣሊያኖች ከፈጸሙት መከራና ስቃይ ጋራ ስናነጻጽረው፤ ወያኔዎች የፈጸሙት ከተመሳሳይነቱ እጅግ የራቀ፤ የባሰና የከፋ እንደሆነ፤ በዚህ ዘመን ዝም ያላችሁትንና፤ ከህዝብ መካከል የተደበቃችሁትን ካህናት፤ በጣሊያን ጊዜ ዝም ካሉትና ከህዝብ ከተደበቁት ካህናት እጅግ በጣም የከፋችሁና የባሳችሁ ናችሁ።

## <u>ወያኔዎች ከጣሊያኖች ጋራ ያላቸው ተመሳሳይነት፡-</u>

ከወያኔ መስራቾቹ ዓንዱ ኢትዮጵያዊው ዶክተር አረጋዊ በርሄ በንስሀ ተጸጽተው የኢትዮጵያን ህዝብ በግልጽ ይቅርታ ባይጠይቁም፤ በእንግሊዘኛ ከጻፉት መጽሐፋቸው፤ ከዚህ ቀደም ወደ አማረኛ ተርጉሜ፤ ደጋግሜ ያቀረብኳትን አንቀጽ፤ ወያኔዎች ከጣሊያን ጋራ ያላቸውን ተመሳሳይነት ለመግለጽ አሁንም ደግሜ አቀርባታለሁ።

**"ቤተ ክርስቲያኗን ከህዝብ ለይቶ በመምታት ስፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝ ቡ አዕምሮ ላይ ስትቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዞት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው"** የሚል መመሪያ ወያኔዎች አውጀው ለ25 አመታት ህዝበ ክርስቲያኑን በተለይም በወልቃይት አካባቢ ያሉትን የታሪክ ነጋሪዎችን መፍጀታቸው ጣሊያንን ያስመስላቸዋል።

ይህን የጥፋት መርሆ  አቶ ሽፈራው ሽጉጤም፤  አቶ ስብሀት ነጋም ያላንዳች ሀፍረትና ይሉኝታ በድፍረት ተናግረውታል። አቶ ታምራት ላይኔም፤ አማራው በጨለንቆ ገደል እንዲወረወር የሰጡት ነፍሰ ገዳይ አመራር ይህንኑ ነበር። ከዚህ ሁሉ ጋራ፤ ድንበር እያፈረሱና ህዝቡን በጎሳና በቋንቋ እየከፋፈሉ፤ እርስ በርስ በመጠራጠር እየጣሉ የተከበረችውን ባንዲራ እያቃጠሉ ወደ ቤተ መንግስት መግባታቸው ተዳምሮ፤ ወያኔዎችን ከጣሊያን ጋራ አንድ ያደርጋቸዋል።

ይልቁንም ጣሊያኖች ከወያኔዎች ሚሻሉባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለቀው እንዲወጡ ዓለም ሲፈርድባቸው፤ ላለመልቀቅ እንደወያኔዎች በልማት ላይ ነን  ቢሉም፤ ጣሊያኖች የራሳቸውን  ቴክኖሎጅ ከባህር ማዶ በመርከብ እየጫኑ  አምጥተው፤ ብዙ ህንጻዎች ድልድዮች በመስራታቸው ጣሊያኖችን ከወያኔወች እጅግ የተሻሉ ከሚያደርጓቸው ብዙ ነገሮች አንዱ ነው።

**<u>ጣሊያን በኢትዮጵያ ላይ ከፈጸመ መከራና ግፍ ወያኔዎች የፈጸሙት ግፍና መከራ ይከፋል።</u>**

የነበሩትን የፋብሪካ መሳሪያዎች ከመሀል አገር  ነቃቅለው መውሰዳቸው፤ ቆዳችንን ቋንቋችን መጠቀማቸው፤ እኛን መሰለው አዘናግተው በመግባት  ድንበር ማፍረሳቸው፤  እርስ በርስ ማጋጨታቸው፤ በቀለም በቋንቋ እኛን የማይመስሉን ጠረፍ አቋርጠው  ባህር ተሻግረው ከመጡብን ጣሊኖች፤  ወያኔዎችን የከፉ  ያደርጋቸዋል።

በዚህ ሁለንተናዊ አስመሳይ ባህርያቸው፤ ቅኝ ገዥ ሆኖ ከመጣው ጣሊያን ለይቶ ለዓለም ለማሳየት ኢትዮጵያውያንን እጅግ አስቸግሯል። ወያኔዎች ስሜታቸው የጣሊያን ቢሆንም፤ በቀሪው ሁለንተናቸው ኢትዮጵያውያን ስለሆኑ፤ የውጭ ታዛቢም ወራሪዎች ናቸው ብሎ ለመቀበል ተቸግሯል። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ ከወያኔዎች ለመላቀቅ፤ ከጣሊያኖች ለመላቀቅ ካደረገው ጥረት በእጅጉ ከብዶበታል። በጣሊያን ከተሰቃየበት ይልቅ በወያኔዎች የተሰቃየበት ዘመን ረዝሞበታል። ወያኔዎች በዚህ ውስብስብ ሰይጣናዊ መርሆዋቸው፤ ኢትዮጵያንና ህዝቧን  ከጣሊያን የበለጠ ጎድተዋል። ጣሊያኖች አገሪቷን ከእጃቸው መዳፍ እንዳትወጣ ለማድረግ ቢሞክሩም፤ ጣሊያኖችን ቀለማቸውና ቋንቋቸው ባእድነታቸውን ስላጋለጠባቸው ብዙ ህዝብ ለመፍጀት  እንደ ወያኔዎች አልቀናቸውም።

ወያኔዎች የጣሊያንን እቅድ ከኢትዮጵያዊ ስነ ልቡና ጋራ በማዋሀድ ለዘመናት የእትዮጵያ ህዝብ አውቆም ሳያውቅም የተቀላቀለውን ህዝብ በግድ አላቀቁት በተኑት አፈረሱት። እስከ ደርግ ዘመን የነበረውን የኤርትራን ህዝብ ከያለበት እያነቁ ከንበረቱ እያፈናቀሉ በዚያው በሚያውቁበት ቋንቋ ከአማራውና ኮአረሞው ከጉራጌውና ከቀረው ህዝብ ጉያ እየመነጠሩ እያነቁ እንዳበረሩት፤  በአልጠግብ ባይ ስግብግብ ባህርያቸው የቀረውን

የኢትዮጵያ ህዝብ ከያለበት ከኖረበት ከተወለደበት፤ አፈናቀሉት። ዘረፉት። ንብረት አልባ ቤት አልባ አደረጉት።

የኢትዮጵያ ህዝብ "ቀኝህን ቢመታህ ግራህን ስጠው። ልብስህን ቢገፍህ መደረቢያህን ስጠው። የተወሰ ርቀት ቢወስድህ፤ እጥፍ አብረኸው ሂድ" (ማቴ 5፡38__42) በሚለው ክርስቶሳዊ መመሪያ 25 ዓመታት ወያኔዎችን በትእግስት ተከተላቸው። ወያኔዎች ይህን ትእግስ ወደ ፍርሀትና ሞኝነት መነዘሩት። ትእግስቱንም አስጨረሱት።

የኢትዮጵያ ህዝብ "መዓቱ ለብእሲ ኢያጌብሮ ጽድቀ እግዚአብሔር" በሚለው በቅዱስ ያዕቆብ ምክርና ተግሳጽ ቁጣውንም የሚገታ ህዝብ ነው። በዓለም ከሚታየው ህዝብ እጅግ በላቀ በመጠቀና በረቀቀ ልዕለ አዕምሮ ቀጸላ የተቀዳጀ። በማይፈታና በማይላላ ቅናተ አዲም (የውሳኔ ትጥቅ) ህሊናውን የታጠቀ ነው። "እንዳንተኩስብህ አትተኩስብን፤ እንዳንገልህ አትገደለን" እያለ ምክርን ትምህርትን በመስጠት ጉዳቱን ሀዘኑና ብሶቱን "ሰማይ ስሚ! መሬትም አድምጭ! የምድር መሰረቶችም ይንቀጥቀጡ! እያለ" ለፈጣሪና ለተፈጥሮ ድምጹን በማሰማት በግርማ በሞገስ በሞራል የሚተም ህዝብ ነው።

በልዩ ሰብአዊ ግርማና ሞገስ በመትመም ላይ ባለው በዚህ ክቡር ህዝብ ላይ፤ ጥይት እንዲተኮስ የሚያዝዝና ትእዛዝ ተቀብሎ የሚተኩስ፤ "ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ በሰላ ሰይፍ ላይ ብትቆም ላንተ ይብስሀል" እያለ በተናገረው ክርስቶሳዊ ድምጽ፤ ከተግሳጽና ከውገዛት እጅግ በሚከፋው ውግዘት "ጥቁር ውሻ ውለድ" ተብሎ ከቀረው ህዝብ ተለይቶና ተቆርጦ መጣል አለበት።

ይህ ህዝብ "ሰማይ ስሚ! መሬትም አድምጭ! የምድር መሰረቶችም ይንቀጥቀጡ! እያለ" ብሶቱን ለማንም ሳይሆን ለፈጣሪና ካባቶቹ ለተረከበው ውርስ (ልዕለ አዕምሮው) ለመግለጽ ከዳር እስከዳር እየተመመ ባለበት ወቅት፤ በትግራይ ህዝብ ስም ራሱን ያደራጀው በህዝብ መካከል የሸፈተው ወንበዴ እንዳይተኩስ፤ መንፈሳውያን መሪዎች ሽማግሌወች ተማርን የምትሉ ሁሉ የወያኔ ምስለኔዎች ድምጻችሁን ከባህታዊ አምኃ ኢየሱስ ድምጽ ጋራ አዋህዱ።

የለሊት ጨለማ አልፎ፤ የጧት ጮራ በፈነጠቀችው ብርሃን ተንተርሰን "አድህን እግዚኦ ዛተኒ ሀገረ ወካልአተኒ አህጉረ ወበሀውርተ እለ በሃይማኖተ ዚአከ የሀድሩ ውስቴቶን። ቅዱሳነ አድህን እምድልቅልቅ ወእምረሀብ ወእመራደ ካልዕ ህዝብ" (399 ሊጦን ዘነግህ)። እያለን የምናቀርበውን ጸሎት መመሪያችሁ በማድረግ ባህታዊ አምኃ ኢየሱስን ተከተሉ።

ይህም ማለት "ያልጋበዝናቸው ህዝቦች እኛንም የሚያጎራብቱንን ወገኖቻችን ወረሩን። ከወረራቸውና ካመጡብን ሽብርና አለመረጋጋት አድነን፤ እነሱ በፈጠሩብን ቀውስ ከደረሰብን ረሀብ ጽምና ርዛት ገላግለን"

"የኢትዮጵያን ህዝብና ቤተ ክርስቲያን ሰበርኳቸው" እያለ በመፎከር ከቤተ መንግሥት ሰርጎ ገብቶ፤ በህዝብ ላይ ከሸፈተው መንግስት ጋራ ተባብራችሁ ለ25 ዓመታት የተጓዛችሁ ካህናት፤ ማፈር ሲገባችሁ፤ የተሰበረችውን ቤተ ክርስቲያን ወክላችሁ ከወያኔ ጋራ በመሰለፍ ታቦትና መስቀል ተሸክማችሁ ብቅ ማለታችሁ በቤተ ክርስቲያንና በህዝብ ላይ የፈጸማችሁትን በደልና ግፍ የበለጠ እጽፍ ድርብ እንዳደረገው ተረዱ ።

በነ ኮረኔል ደመቀ ላይ የተደረገውን ይህን መሳይ አዚም፤ የሞሰለኒ ካህናትም በነበላይ ዘለቅ ላይ ለማድረግ ሞክረዋል። የነበላይን ክርስቶሳዊ ስነ ልቡና በስለላ የተረዱ ጣሊያኖች፤ በነበላይ ሲማረኩ፤ "በማርያም አትጨክኑብን" ሲሉ፤ በላይ ዘለቀ፤ "የኔ ማርያም ትቢተኞችን በተናቸው፤ የተዋረዱትን የተገፉትን የተበደሉትን የወደቁትን አነሳቸው" የምትል እንጅ ፤ የሰው አገር ውረሩ የምትል አይደለችም። የቅድስት እመቤቴን ስም ማታልያ በማድረጋችሁ ተጋደሙና ተገረፉ" እንዳለ፤ ዛሬም ታቦት ተሸክማችሁ ስእል መስቀል ይዛችሁ ለማዘናጋት ወደህዝብ ስትንከረፈፉ፤ የጎንደር ህዝብ ወያኔ ያነደደበትን እሳት ሳያስቀድም፤ በኦሮሞው ወንድሙ ላይ የሚያነደውን እሳት አቁም እያለ የተመመው የጎንደር ህዝብ ተጋድማችሁ ልትገረፉ ይገባችኋል አላለም። አለማለቱም ከዚህ ቀደም አባቶቹ እነ አጼ ቴወድሮስ፤ እነ ፋሲል ያደረጉትን አስተዋይነትና ያሳዩትን መድምም በታሪካዊቷ ጎንደር ከተማ ላይ ደገመው።

**"ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው።"** የሚል መርሆ ወያኔ ዘርግቶ ለ25 አመታት ሲደበድብ የኖረውን ህዝብ፤ ዛሬም ንስሀ ግባ የምትሉ ካላችሁ፤ ተመሳሳይ ውርደትና ቅጣት ሳይደርስባችሁ መስመራችሁን ከባህታዊ አምኃ ኢየሱስ ጋራ አስተካክሉ።

"ቤተ ክርስቲያንና ህዝበ ክርስቲያኑን ሁሉ ሰበርኩት" እያለ ግፍ ሲሰራ፤ በኦረሞ ስም አማራውን ሲገድል የነበረው የወያኔ መንግስት ከቤተ መንግስት ለቆ ንስሀ እንዲገባ መንገር ሲገባችሁ፤ ታቦት ተሸክማችሁ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ስም ወደ ህዝቡ የምትመጡ ካህናት እራሳችሁ ንስሀ ግቡ! በህዝብ ፊት ለመቆም ትበቁ ዘንድ መጀመሪያ ከህዝቡ ያጣችሁትን መታመን መልሱ! ከዚህ መንግስት ጋራ የተሳሰራችሁበት ሰንሰለት የተበጠሰ መሆኑን ለህዝቡ ግልጽ አድርጉ።

መንፈሳውያን ነን፤ ሽማግሌዎች ነን  የምትሉ የትግራይ ተወላጆች ንቁ! ጣሊያን ባልተወለደ  አንጀቱ የኢትዮጵያን ህዝብ በመርዝ ጢስ ከፈጀው ይልቅ፤ ወያኔ በስማችሁ ተደራጅቶ መካናይዝድ በሆነ ወታደር ለ25 አመታት የፈጀው ኢትዮጵያዊ ወገናችሁ ስፍር ቁጥር የለውም።

የትግሬ ደም የሌለበት አማራ የለም። ያማራ ደም የሌለበት ኦረሞ ጉራጌና ሌላም ዘር የለም። ተቀላቅሎ ለዘመናት ተስማምቶና ተዋዶ ተጋብቶ ተዋልዶ የኖረውን ህዝብ ዘርንና ቋንቋውን በመጠቀም ከፋፍለው ግፍ ሲፈጽሙ የኖሩት ጥቂት ወያኔዎች ማጣፊያው ሲያጥራቸው፤  የቂምና የጥላቻ መርግ እዳቸውን፤  እዳ በደል በሌለበት በንጹሁ ኢትዮጵያዊው የትግራይ ህዝብ ላይ ጭነው፤ የዘሩፍትን ይዘው መሸሻቸው የማይቀር ነው። የመለሰን  ቅዠት  ራእይ እያላችሁ፤ ህዝብ ከወደቀበት መሪር ያገዛዝ ቀንበር እንዳይላቀቅ፤ ጊዜውን ያራዘማችሁ፤ አሁንም  በማራዘም ላይ ያላችሁ፤ ካህናት፤  ምሁራን፤ የጥበብ ሰዎች ነን የምትሉ ሁሉ በጥልቅ እንድታስቡበት፤  “ዑቅ እንከ ርእሰከ በእንተ አንብቦ ወዘልፈ ኅሉ ባቲ ። ወእመሰ ገበርከ ዘንተ ታድህን ርዕሰከ ወዘሂ ይሰምአከ”(1 ጢሞ 4፡16) በሚለው በቅዱስ ጳውሎስ ምክርና ተግሳጽ እማጸናችኋለሁ። ይህም ማለት ”ለራስህ ለተልእኮህ ተጠንቀቅ። በተግባርም ግለጸው። ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህ”

**“ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝ ቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው”** የሚለውን ያቶ መለሰን  ራእይ መንቀፍ ፖለቲካ መግባት ነው፤  ከሚለው ከነ አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ አዚምና ቅዠት ተላቀቁ! በወያኔ መንግሥት በተበደለው በጎንደር ህዝብ መካከል ቆመው ባህታዊ አምኃ ኢየሱስ ያሰሙትን ድምጽ አስተጋቡ ! ባህታዊ አምኃ ኢየሱስ በከፈቱት በር ግቡ! ይህ የባህታዊ አምኃ ኢየሱስ ድምጽ በጣሊያን ወረራ ጊዜ የተሰማውን የእነመምህር ገብረ ኢየሱስን ድምጽ እያስተጋባ ነው !  እናንተም ንስሀ ገብታችሁ የባህታዊ አምኃ ኢየሱስን ድምጽ ብታስተጋቡት በመጨረሻ  ከሚመጣው መከራ ራሳችሁንም የሚሰማችሁን ወገንም ታድናላችሁ።

“ገአረ ኢየሱስ ኀበ አቡሁ፤ ወኀበ አዳም ገብሩ” ብሎ ቅዳሴያችን እንደሚነግረን የባህታዊ አምኃ ኢየሱስ ጥሪ፤ አዚም የሚገፍ ከቅዥት የሚያላቅቅ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ ያሰማው ድምጽ ነው። ህዝብ የሚያሰቃየውንና የሚገለውን ወያኔን፤ እንደ ባህታዊ አምኃ ኢየሱስ አትግደል የሚሉትን ፖለቲካ ገባችሁ የምትሏቸው ሁሉ፤ ከክርስትና በተለይም ከኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርትና  መመሪያ እጅግ የራቃችሁ መሆናችሁን ተረዱ ! ይህ ከጎንደር ህዝብ ድምጽ መካከል ዘልቆ የተሰማው የባህታዊ አምኃ ኢየሱስ ድምጽ፤ በጣሊያን ጊዜ በጥቅምና በሹመት የታሰረውን፤  ፍርሀቱን በጸሎተኛነት የሸፈነውን፤

ሳያመው ሳይደክመው አሞኛል ድክሞኛል እያለ የተኛውን ለመቀስቀስ እነ መምህር ገብረ ኢየሱስ ያሰሙት ድምጽ ነው። የባህታዊ አምኃ ኢየሱስ ድምጽ በወያኔ ዘመን በፍርሀት የፈዘዘውን፤ በጥቅም የደነዘዘውን ሁሉ ካህን ሰባኪና ባህታዊ የሚቀሰቀስ የጥሪ ድምጽ ናትና ትድረሳችሁ